# ከድጡ ወደ ማጡ የሆነው
# የአርሶ አደሩ ኑሮ

(አብርሃም አየለ)

በወርሃ ሐምሌ አገርንና ቤተሰብን ለመጎብኘት በየሁለት ዓመቱ እንደምናደርገው ሁሉ ዘንድሮም በአንድ ከተማ አብረን ከምንኖር ጓደኛዬ ጋር ሆነን ወደ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ ሄደን ነበር። ታዲያ መጠነኛ ቆይታ በአዲስ አበባ ከአደረግንና ለመስክ የሚሆን መኪና ከተከራየን በኋላ ለአንድ ሳምንት ጉብኝት ወደ ባህር ዳር ሄድን። ጉዞአችንንም በሱሉልታ አቅጣጫ ጀመርን። ደብረ ሊባኖስንና ፍቼን አለፍን፣ በዓባይ ድልድይ ስር ቡና ጠጣን፣ ደጀን ቁርስ በላንና ደብረ ማርቆስ ደረስን።

ወቅቱ ክረምት እንደመሆኑ አካባቢው አረንጓዴ ተላብሶ መመልከት ደስታን የሚሰጠውን ያህል ስሙ ብቻ የተረፈን ዓባይ ደግሞ ከደጋው የአገሪቱ ክፍሎች ያሰባሰበውን ደለልና ውሃ ሞልቶ ሲጎዝ ማየት በመጠኑም ቢሆን ያስቆዝማል፤ የቁጭት፣ የሃዘንና የንዴት ቁዘማ። በደብረ ማርቆስ ከተማ በሚገኝ <ሸበል> በተባለ ሆቴል ምሳ በልተን ትንሽ እረፍት ከአደረግን በኃላ ጉዞ በመቀጠል ከከተማው 30ኪ.ሜ እርቆ ከሚገኘው አማኑኤል ከተባለ አነስተኛ ከተማ ስንደርስ ሶስት ሰዎች ወደ ደምበጫ እንድንወስዳቸው ጠየቁን። በቂ ቦታ ስላለን እንዲሁም የአካባቢውን ሁኔታ ይበልጥ ለመረዳት ከነዋሪው ጋር መወያየት ይረዳል በማለት አሳፈረናቸውና ጉዞ ቀጠልን።

ወዴትና ለምን እንደሚሄዱ÷ ኑሮ እንዴት እንደሆን÷ ክረምቱ ለአዘመራው ተስማሚነቱ ምን እንደሚመስልና ሌላም ሌላም እያነሳን ጨዋታ ቀጠልን። እለቱ ረቡዕ እንደመሆኑ የሚሄዱት በደንበጫ የገበያ ቀን ስለሆነ ለአረቄ ግብዓት የሚሆን ማሽላ ለመግዛት እንደሆነ ተረዳን። አቶ አበበ አባወራው ሲሆን ባለቤቱ ወ/ሮ የኔዓለም ትባላለች። ሶስተኛዋ የአስራ ስምንት ዓመት ዕድሜ ያላት ልጃቸው ናት። ወ/ሮ የኔዓለም በተላበሰችው የኑሮ ጉስቁልና የስድሳ ዓመት ሰው ትመስላለች ግን የአርባ ዓመት ወይዘሮ መሆኗ ተነገረን። የለበሰችው÷ የአካል ሁኔታዋ÷ ጫማ የማያውቀውና ንቃቃት የሸፈነው እግሯ የቤተሰቡ ኑሮ ጐስቋላ መሆኑን ይመሰክራል። ወሬያችን ቀጥሎ ወጣቷ የሺን በመጠኑም ቢሆን አወጋናት -

<የሺ፣ ትማሪያለሽ?>

<እማር ነበር፤ ስምንተኛ ክፍልም ደርሻለሁ፤ ግን ትምህርቱ ከበደኝና አቆምኩ።>

<አንቺን የመሰለ ጎበዝ አይከብደውም፤ በርቺና ትምህርትሽን ቀጥይ።>

<እሺ!>

ስለትምህርት ጠቃሚነት÷ ከድህነት ለመላቀቅ ዋናው መሳሪያ ስለመሆኑ÷ ሌላም ሌላ የሺ ይገባታል ብለን ባሰብነው አገላለፅ ለማብራራት ሞከርን። ከየሺ አመላለስና ከፊቷ ከሚነበበው ገፅታ አንፃር እናትና አባቷ ፊት ለመናገር ያልፈለገችው ነገር እንዳለ ያስታውቃል። ከእሷ ጋር የሚደረገውን ውይይት አቆምንና ገበሬ የሆነወን አቶ አበበን ስለ አዝመራ÷ ስለ ወቅቱ የምርት ይዞታ ጠየቅነው -

<ምን ዋጋ አለው!> በሚል የምፀት ስሜት ነበር ጥያቄውን የመለሰው፤ በማስከተልም፣

<አርሰናል÷ ዘርተናል÷ ግን የፈረንጅ ቀላቢ ነው የሆነው> በማስከተልም <እንዲያው እውነቱን ለመናገር> አለ ገበሬው አበበ በተኮሳተረና ፀፀት በተላበሰ ስሜት <እውነቱን ለመናገር በቅኝ ገዥዎች አልተያዝንም ለማለትም አልደፍር …. . >

አባባሉ አስደንጋጭ ከመሆኑም በላይ ከአንድ ገበሬ ያልጠበቅነው ገለፃ ስለነበር <እንዴት?> በሚል አጭር ጥያቄ ነበር ገለፃውን እንዲቀጥል የጠየቅነው።

<ማዳበሪያ!> አለ፤ ቃሉን ሲጠራው የሀዘንና የቁጭት ስሜት ይነበብበታል።
<የምናርሰው÷ የምንዘራው÷ የምናጨደውና ወቅተን ለገበያ የምናቀርበው በላያችን ላይ የሚናጥጠውን የማዳበሪያ እዳ ለመክፈል ነው - ወንድሞቼ እንዲያው እስኪ ገበሬውን ጠይቁት - ደክሜ አምርቼ ኑሮዬን አሻሽላለሁ የሚለው ተስፋውና ምኞቱ ተሟጦ አልቋል፣ የማዳበሪያ እዳዬን እንዴት እከፍላለሁ የሚለው ጭንቀት ብቻ ነው የቀረው።>

የአቶ አበበን ንግግርና ብሶት ከሰማን በኋላ <ታዲያ አንተ ወይንም በአጠቃላይ አርሶ አደሩ መፍትሔ ይሆናል ብላችሁ የምታስቡት ምን ይሆናል?> ብለን ጠየቅነው። ገበሬው አበበ ይህንን ለመመለስ ብዙም ማሰብ አላስፈለገውም ፍርጥም ባለ ስሜት <መንግሥት ድጎማ ቢያደርግልን ይህ የመጀመሪያው ነው ቀጥሎ የማዳበሪያ ፋብሪካ እዚሁ አገራችን ቢቋቋም ዋጋው ይቀንስልን ነበር። አሁን እኮ የምንከፍለው በኩንታል ወደ ስምንት መቶ ብር ይጠጋል። እንግዲህ እግዜር ያሳያችሁ ግማሽ ሄክታር ከሚሆን መሬት ምርት ተመርቶ የማዳበሪያ ተከፍሎ - እንዴት ነው ኑሮን የምንኖረው?> በማለት ነበር ያብራራውና ጥያቄውን በጥያቄ የመለሰው። እንግዲህ አርሶ አደሩ የአጭርና የረጅም ጊዜ መፍትሔ ማቅረቡ ነው።

ደምበጫ ለመድረስ ጥቂት ሲቀረን ጨዋታችንን ለማሳረግ <የዘንድሮን ምርጫ በተሳካ ሁኔታ እንዳለፈ ሰማን፤ እናንተም ደህና አድርጋችሁ መረጣችሁ አሉ> ብለን ለመናገር የፈለግነውን ሳንጨርስ ሶስቱም ሊቆጣጠሩት ባላቻሉት ሳቅ ተጠመዱ። ሳቃቸው ጋብ እስኪልላቸው ለደቂቃ ያህል መቆየት ነበረብን። ትንፋሹን መለስ ያደረገው አቶ አበበ <ጌታው - እውነትዎን ነው - እንዲያው ሌላ ሌላ - ደግ ደጉን ብንጫወት ይሻላል> በማለት ነበር ጨዋታውን እንድንለውጥ ያደረገን።

ደምበጫ ደርሰን ተሳፋሪዎቻችንን ለመሰናበትና ገበያውንም ለመመልከት እንዲሁም ወጣቷ የሺን ለማነጋገርና ስለእሷ ይበልጥ ለመረዳት ወደ ገበያው አብረን ዘለቅን። አንዳችን አባትና እናትን አንዳችን ደግሞ የሺን አነጋገርን። የሺ ከማንም የማያንስ የብሩህ አዕምሮ ባለቤት እንደሆነች ለመገንዘብ ብዙ ግዜ አይወስደም። የምትሰነዝራቸው አስተያየቶችና የምታደርገው ገለፃ ይህንኑ ያረጋግጣል። የእሷ ትምህርት ማቆም - ትምህርቱም <የሚከብዳት> ምክንያቱ የሚከተለው ነው÷

እናቷ አረቄ እያወጡ ለነጋዴ ስለሚሸጡ ይህን ስራ ማገዝ አለባት። አባት በእርሻ በሚሰማራበት ጊዜ ምሳ ሰርቶ የመውሰድ እንዲሁም በአረም÷ በጉልጓሎና በአጨዳ መርዳት÷ እንደዛሬው ሁሉ ረቡዕ በሚውለው ገበያ በመሄድ ለአረቄ የሚሆን ግብዓት መግዛትና መሸከም ይጠበቅባታል። ሃላፊነቷና ስራዋ ብዙ ነው። <ቀኑ 24 ሳይሆን 48 ሰዓት ቢሆንም የኔ ስራ አያልቅም> በማለት ነበር ያአለባትን የኑሮ ሸክም የሺ የገለፀችው።

<እንግዲህ እንዴት አድርጌ÷ ምኑ ከምን ሆኖልኝ ጥናቴን ላጥና፤ ትምህርት ቤት መሄድ ብቻ በቂ አይደለም። እሱም ቢሆን ከትምህርት ቤት የምቀርበት ግዜም የበዛ ነው። እንግዲህ ይህ ሁሉ ተዳምሮ በትምህርቴ የማገኘው ውጤት እያሽቆለቆለ ሄደ። በግልፅ ለመናገር ሌላም ችግር አለብኝ። ረሃቡም ቀላል አይደለም። በተራብ ስውነት ምን አይነት ትምህርት ተቀባይነት ይኖረዋል። እንደምታዩኝ ልብሴ ሰው ፊት የሚያስቀርብም አይደልም። ከዚህ

ሁሉ ትምህርቴን ማቆም ይሻላል ብዬ ነው ጋሽዬ> በማለት ነበር የሺ ያለችበትን ሁኔታ ያብራራቸው። በማስከተልም እንዲህ አለች፦ <ቅድም ጓደኛህ ስለ ትምህርትና ጥቅሙ ጥሩ ጥሩ ነገሮችን ሲናገር በደንብ ሰምቼዋለሁ። ያገሬ ሰው <እዬዬም ሲዳላ ነው ይላል።> እንደነገርኩህ ይህንንማ መቼ አጣሁት ችግሬ ችግር ሆኖ እንጂ።> በማለት ነበር ሃዘን በተላበሰ ስሜት ገለፃዋን የደመደመችው። የአገራችን የገበሬ ሕይወት፣ መንግሥታት ቢቀያየሩም፣ አርሶ አደሩ የልማት መርሃግብራቸው መሰረት ነው ቢሉም፣ ምንም አለመለወጡ በጣም የሚያሳዝን ነው። ከማሳዘንም አልፎ የሚያስገርመው ደግሞ፣ በአገሪቱ ከሚገኙ ጥቂት ትርፍ አምራች ከሚባሉ አካባቢዎች አንዱ ጎጃም ሲሆን የዚህም አካባቢ ነዋሪ ይህን በመሰለ የተጎሳቆለ ሕይወት መገኘቱ ነው።

የዚህ ቤተሰብ ኑሮ የሚያሳዝንና የአብዛኛውን የአገራችንን አርሶ አደር ህልውና የሚወክል እንደሚሆን መገመቱ አዳጋች አይሆንም። የወጣቷ የየሺ የወደፊት ዕጣ ፈንታስ ምን ሊሆን ይችላል። ልክ እንደእናቷ እሷም የኑሮ በትሩን ተቀብላ ሽክርክሪቱን መቀጠል? ምናልባትም ለወጥ ያለ መስመር ከአገኘችም ከተማ ገብቶ የመጠጥ ቤት አሳላፊ መሆን? ከዚህ ያለፈና በቅርፀ ካልሆነ በይዘቱ ብዙም ለውጥ የሌለው ህይወት እንደሚጠብቃት ገመትን። በተጠቀሰው አካባቢ ዕቃ ተሸክመው ወገባቸው ጎብጦ፣ ሰውነታቸው ኮስሶ የሚታዩ ሴቶች መንገዱን ሞልተውታል። ወንዶችን መሸከም ባህሉ <አይፈቅድላቸውም>። የሥርዓተ ፆታ ባለሙያዎች በህብረተሰቡ ተንሰራፍቶ የሚታየውን ጎጂ ባህላዊ ልምዶች ለማስወገድ ትምህርት በመስጠት በኩል ብዙ እንደሚጠበቅባቸው ተወያየን።

በደምበጫ ከተማ ከነአቶ አበበ ጋር ገበያውን ለግማሽ ሰዓት ከተመለከትንና ብዙም እርቆ በማይገኘው <መላክ ሆቴል> ቆይታ አድርገን ወደ መኪናችን እንደተመለስን ገበያቸውን ጨርሰው የሚመለሱትን እነ አቶ አበበን ከርቀት አየናቸው። ወ/ሮ የኔዓለምና የሺ የተሸከሙት፣ እንኳንስ ያንን ያህል መንገድ ለመጓዝ ጥቂት እርምጃዎች ለመራመድም የመሚከብድ ይመስላል። ወደ መጡበት ለመሸኘት ብዙም አላመነታንም፤ ምክክርም አላስፈለገንም። ይበልጥ ተዋውቅን ይበልጥም በግልፅነት እያወጋን ጉዞ ቀጠልን።